ኢትዮጵያዊ አሜሪካውያን ማኅበረሰብ
**Ethiopian American Community**
4356 Wilson Ave. # 1 San Diego CA 92104 Tel./Fax: (619) 563-5741

June 18, 2009

## የ26ኛው ዓመት የኢትዮጵያ ስፖርት ፌደሬሽን በሰሜን አሜሪካ
## ቺካጎ ከተማ June 26 – July 4, 2009

==========================================================================

የሁሉምና ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ማእከል የሆነ በየዓመቱ አንዴ የሚዘጋጀው የስፖርትና ባሕል ፌስትቫል ዘንድሮ በኢሊኖይስ ስቴት በቺካጎ ከተማ የተለመደ መስተንግዶውን አዘጋጅቶ ውድ ኢትዮጵያውንና የኢትዮጵያ ወዳጆችን ይጠብቃል።

### ቺካጎና መስተንግዶው

ኢትዮጵያውያን ከሚኖሩባቸው የአሜሪካ ከተሞች እጅግ በጣም የላቀና ጠንካራ የኢትዮጵያውያን ማኅበረሰብ (Community) መሰረቱን የጣለባት ቺካጎ ከተማ የብሉ ናይል ክለብ አመራርና በዶክተር እርቁ ይመር በሚመራ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ትብብር ለመጀመሪያ ጊዜ በሚድ ዌስት ማለት በቺካጎ ከተማ በዝግጅት ላይ የሚገኘው የስፖርትና የባሕል ፌስቲቫል ቅድሚያ ለእንግዶች በሚል መርዕ ፕሮግራሙ ሶስት ታዋቂ ሆቴሎችን በቅናሽ ዋጋ፣ እንዲሁም የሕዝብ ትራንስፖርት ከሆቴሎች እስከ ስታዲዮም ድረስ፣ ማንኛውንም የንግድ ትርኢትና አትራፊ ያልሆኑ ተቋማት ማንነት መግለጫ ቦታዎችን አዘጋጅቶ ይጠብቃል።

በተለይ ተጫዋቹም፣ አጫዋቹም፣ አዘጋጁምና ተመልካቹም መላው ኢትዮጵያዊ በናፍቆት የሚጠብቀውን <u>የኢትዮጵያን ቀን</u> በላቀና በደመቀ ሁኔታ ለማክበር የታዋቂው ድምፃዊ ዶ/ር ጥላሁን ገሰሰ መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ...

1. ታዋቂ ድምጻዊያን የሚሳተፉበት የሙዚቃ ፌስቲቫል
2. የዶ/ር ጥላሁን ገሰሰ መታሰቢያ ልዩ ዋንጫ
3. የተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰብ ባሕላዊ የሙዚቃ ቴርኢት በማዘጋጀት

እንዱሁም በዕለቱ ሐገር የሚታወስበት፣ አንድነት የሚታደስበት፣ ሙታን የሚታሰቡበት፣ ሕያው የሚሸለሙበት ከፍተኛ ሐገራዊና ወገናዊ መድረኮች የሚከወኑበት ፌደረሽኑ ያዘጋጀ መሆኑን እየገለጽን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ከላይ በተጠቀሱት ቀናት በቺካጎ ከተማ ተገኝተው የፌስቲቫሉ ተሳታፊ እንደሚሆኑ እንመናለን።

EthiopianAmerican.com